The Federal ... Republic

Ethiopian ... Authority

1-0/789/09

0.4 ጥር 2009

**በዝርዝር ለተመለከቱት**

**<u>በያሉበት</u>**

**ጉዳዩ:- <u>የመመሪያ ቁጥር 112/2008 አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ(3) መሻሻሉን ስለማሳወቅ</u>**

ስለ ጉምሩክ ጥፋቶች አስተዳደራዊ ቅጣትና የዕቃ ውርስ አፈፃፀም በወጣው መመሪያ ቁጥር 112/2008 አንቀጽ 21(3) መሠረት ባለንብረቱ እያወቀ የኮንትሮባንድ ዕቃ ጭኖ የደተገኘ ተሽከርካሪው የሚወረስበት ሁኔታ ተደንግጎ ይገኛል፡፡

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 147(3) (ለ) መሠረት " የማጓጓዣው ባለቤት ሆኖም ሆኖም ተገቢውን እርምጃ ሳይወሰድ ከቀረ" እያወቀ የድርጊቱን መፈፀም ለመከላከል ወይም ለማስቆም ተገቢውን እርምጃ ሳይወሰድ ከቀረ" የሚለው የህጉ አገላለፅ የማጓጓዣው ባለቤት የድርጊቱን መፈፀም ያውቅ እንደነበር በቅድሚያ በማስረጃ ማረጋገጥን የሚጠይቅ ቢሆንም የተሽከርካሪው ባለንብረት በተደጋጋሚ በተሽከርካሪው የኮንትሮባንድ ወንጀል የሚፈፀም መሆኑን እየተገለፀለት ተገቢውን ቁጥጥር ለማድረግ አስፈላጊውን እርምጃ ካልወሰደ ወንጀሉን ለመከላከል ዝግጁነትና ፍላጎት እንደሌለው ስለሚገመት ከማስጠንቀቂያ በኋላ አስቀድሞ ስለሚቆጠርና የጥቅሙም ተካፋይ እንደሆነ ስለሚገመት ከማስጠንቀቂያ በኋላ አስቀድሞ ማስጠንቀቂያ በተሰጠበት ተሽከርካሪና ሾፌር ተጨማሪ የኮንትሮባንድ ወንጀል ተፈጽሞ ከተገኘ ይህንኑ ተሽከርካሪ መውረስ ተገቢ መሆኑ ታምኖበታል፡፡

ከዚህ አኳያ የመመሪያ ቁጥር 112/2008 ንዑስ አንቀጽ (3) መሻሻል ያለበት ሆኖ ስለተገኘ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

"3/ ከማስጠንቀቂያው በኂላ አስቀድሞ ማስጠንቀቂያ በተሰጠበት ተሽከርካሪና አሽከርካሪ በድጋሚ የኮንትሮባንድ ወንጀል መፈፀሙ የተረጋገጠ እንደሆነ የተሽከርካሪው ባለንብረት ወንጀሉ መፈፀሙን እያወቀ ድርጊቱን ለመከላከል ወይም ለማስቆም ተገቢውን ጥረት እንዳላደረገ ተቆጥሮ በድጋሚ የኮንትሮባንድ ወንጀል የተፈፀመበት ተሽከርካሪ ይወረሳል፡፡ "

ስለሆነም ከላይ ተሻሽሎ በተገለፀው መመሪያ ቁጥር 112/2008 አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት እንዲፈፀም አስታውቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ከበደ ጫኔ ገብሩ
ዋና ዳይሬክተር/ሚኒስትር

04/05/09

<u>ግልባጭ፣</u>

- ለህግ ማስከበር ሥ/ዘርፍ
- ለጉምሩክ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ሥ/ዘርፍ
- ለጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ ቡድን
  <u>ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን</u>

- ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  <u>አዲስ አበባ</u>
- ለአዳማ ቅ/ጽ/ቤት
  <u>አዳማ</u>
- ለሞጆ ቅ/ጽ/ቤት
  <u>ሞጆ</u>
- ለሐዋሳ ቅ/ጽ/ቤት
  <u>ሐዋሳ</u>
- ለባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት
  <u>ባህር ዳር</u>
- ለመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት
  <u>መቀሌ</u>
- ለድሬደዋ ቅ/ጽ/ቤት
  <u>ድሬደዋ</u>
- ለጅማ ቅ/ጽ/ቤት
  <u>ጅማ</u>
- ለጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤት
  <u>ጅጅጋ</u>
- ለሚሌ ቅ/ጽ/ቤት
  <u>ሚሌ</u>
- ለጋላፊ ቅ/ጽ/ቤት
  <u>ጋላፊ</u>
- ለኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት
  <u>ኮምቦልቻ</u>
- ለሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት
  <u>ሞያሌ</u>
  <u>ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን</u>